# እኛና ጦርነት

ጦርነት አስከፊ አውዳሚና ለሰው ልጆች በአጠቃላይ ሰቆቃ ውጤት ያለው ድርጊት መሆኑን በተግባር ያዩት ቀርቶ በፊልም የተመለከቱትም ቢሆኑ ሳይገነዘቡ የሚቀር አይመስለኝም። በአለም ላይ የተካሄዱ አስከፊ ጦርነቶችን ዛሬ የሆሊዉድ ሰዎች እነደመዝናኛ አድርገው በፊልም ሲያቀርቡት ትውልዱ ጦርነትን በመዝናኛ መልኩም ጭምር ቢመለከተው አስደናቂ አይሆንም። ዛሬ አሜሪካንና አውሮፓን በመሳሰሉ ሃገሮች እጂግ ዘመናዊ የሆኑ በአንድ ጊዜ በርካታ ሰዎችን ህይወት ለማጥፋት በሚያስችሉ መሳሪያዎች በየቀኑ የሽብር ተግባር ሲካሄድ የምናየው የጦርነት ፊልሞችና ያም የፈጠረው ለሰው ልጅ ክቡር ህይወት ደንታ ቢስነት ውጤት ነው። በጦርነት ሰበብ ያደጉ ማለትም (በቴክኒዎሎጂ)እንዳሉ ሁሉ ጦርነት ደግሞ ያቀጨጫቸው ሃገሮች በርካቶች ናቸው። ከነዚህ ሃገሮች አንድዋ ሃገራችን ኢትዮጵያ ናት ቢባል ማጋነን አይሆንም ። ታሪክ መመዝገብ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እንኳን ከሽህ በላይ ጦርነቶችን አስተናግዳላች። አሁን እየደከመ ባለው ትውልድ ዘመን እንኳን ከንጉሱ ስርአት ጀምሮ ቢያንስ ከሃያ በላይ የሚሆኑ ጦርነቶችን አስተናግደናል፥፥

አሁን ባለው ትውልደ እንኳን

በሻቢያና በኢትዮጵያ መንግስት ( በንጉሱ በ ደርግ ዘመን የተካሄደው ጦርነት )

በዋቆ ጉቱ የሚመራው የኦሮሞ ንቅናቄና በንጉሱ መንግስት የተካሄደው ጦርነት

ህዋሀት ኢሃዴግና በኢትዮጵያ መንግስት (ደርግ የተካሄደው ጦርነት

በኦሮሞ ነጻ አውጭ ድርጂትና በደርግ መንግስት የተካሄደው ጦርነት

በአፋር በሲዳማ ነጻአውጭዎችና በደርግ መንግስት የተካሄደው ጦርነት

የታላቁዋ ሶማሊያ መስፋፋት አላማ በንጉሱ በደርግ ዘመን የተካሄደው ጦርነት

ኢህአፓና ኢዲዩ ከደርግ መንግስት ጋር ያደረጉት ጦርነትና እርስ በርሳቸውም ኢሃፓ ወያኔ እዲዩ ያካሄዱት ጦርነት

በወያኔ ኢሃዴግ የስልጣን ዘመን ደግሞ

በህዋሃት ኢሃዴግ መንግስትና በ ኦ ኤል ኤፍ መካከል የተደረገው ጦርነት ዛሬም የቀጠለው ጦርነት

በህዋሃት ኢሃዴግ መንግስትና በኦ ኤን ኤል ኤፍ  መካከል የተደረገው ጦርነት ዛሬም ያለው ጦርነት

በህዋሃት ኢሃዴግ መንግስትና በአልሻባብ እየተደረገ ያለው ጦርነት ዛሬም ያለው ጦርነት

በህወሃት ኢሃዴግ መንግስትና በሻቢያ በሚመራው የኢርትራ መንግስት መካከል እየተካሄደ ያለው ጦርነት

አርበኞች ግንቦት ፯ ( በኤርትራ መንግስት ድጋፍ  የጀመረውና ትኩሱ የርስ በርስ ጦርነት

እነዚህ ጎልተው የታዩና ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን  የሃገራችንን ዜጎች የበሉ ይህ ትውልድ የሚያውቃቸው ጦርነቶች ናቸው

ከሁሉም በላይ በየስራቱ መሳሪያ አንግበው ጦርነት ውስጥ ሳይገቡ በአምባገነናቱ መንግስታት በተለይም  በደርግና ህወሃት ኢሃዴግ   በሰላማዊ ዜጎች ላይ  በየጊዜው የሚፈጸመው እልቂት ኢትዮጵያና ጦርነትን ደም ማፍሰስን  ለይቶ ማየት እንደማይቻል ይህ ትውልድ በሚገባ የሚገነዘበው የመሰለኛል። የኢቲዮጵያውያን የሃገር ምንነት  ስነልቦና የጦርነት ስነልቦና ቢሆን አያስገርምም ። እድሚያችሁ በ ፳ አመት ወይም ከዚአም በላይ ወይም በታች የሆናችሁ ጦርነት የሌለባት ኢትዮጵያን ስለማናውቃትና የኢትዮጵያን እንደሃገር መኖር በደም መፍሰስ ብቻ ስለምናስባት የችግሮች መፍቻ ሌሎች አማራጮችን ማየት ባንች

አያስደንቅም። በኛ ዘመንና በቀደምት አባቶቻችን መካከል ያለው ልዩነት እነርሱ ከጣሊያን ከቱርክ ከእንግሊዝ በአጠቃላይም ከቅኝ ገዝዎች ሃገራችንን ለመጠበቅ የከፈሉት መስዋእትነት ሲሆን በዘመናችን ይህ መሰሉ ጦርነት በጅ አዙርም ይሁን በቀጥታ  ከውጭ ሃይሎች   ጋር ተመሳሳይ ጦርነት ያካሄድነው የመስፋፋት አላማ ዪዛ ከተነሳችው ሶምሊያ ጋር ብቻ ነው። የተቀረው ግን እኛው በእኛው የተጨራረስንበት ጦርነት ነው። ምናልባት ዛሬ ኤሪትራ ሌላ ሃገር እንድትሆን እኛው ወስነን እኛው ፈቅደን የሌሎች የኢትዮጵያን ጥቅም የሚጻረሩ ሃይሎች መሳሪያ  እንድትሆን አድርገን የሁለቱን ወንድማማች ህዝቦች እርስ በርስ እንዲጨራረሱ ያመቻቸነውም እኛው ነን ። ስለዚህ ጦርነቱ የእርስ በርስ ነው። በእርስ በርስ ጦርነት ደግሞ ሃገር ቂምበቀል የቋጠረ ዚጎችን ይዛ ወደፊት መራመድ እንደማትችል እሙን ነው። ስሞኑን በወጣው የአለም አስሩ ደሃ አገሮች ተርታና ረሃብተኛ ከሚባሉት ውስጥም  መገኘታችን ባያስገርምም ያለን ሃብትና ክምችት ለኛ ብቻ ሳይሆን ለአካባቢያችንም የተትርፈረፈ እንደሆነ ብዙ ጥናቶች ያሳያሉ።

እነሆ ዛሬም የርስበርሱ ጦርነት አታሞ ከየአቅጣጫው እየተጎሰመ ነው። ለጦርነቶች ሁሉ ደግሞ መንስኤ አላቸው። በተለይ የርስ በርስ ጦርነት ትልቁ ምክንያት በአንድ ሃገር ውስጥ ያለው ስራት ኢፍትሃዊነት ኢዲሞክራሲያዊነት መሆኑ አያጠያይቅም ። በህዝቦች መካከል መተማመን በመንግስታትና በህዝብ መካከል ጤናማ ግንኙነት እስካለ ድረስ የርስ በርሱ

ጦርነት አይታሰብም ። ምክንያቱም በተፈጥሮ የሰው ልጅ በሰላም ኖሮ በሰላም መሞትን ዪመርጣል። ከሰው ልጆች ውስጥ ጥቂቶች ከግል ስግብግበነት ወይም በስልጣን ጥቅም ታውረው ዜጎችን እርስበርስ በማባላት የስልጣን ዘመናቸውን ለማርዘም በሚያድርጉት ኢፍትሃዊ ጉዞ ለኢፍትሃዊነታቸው የተለያዩ ካባዎችን በሚደርቱ የፕሮፓጋንዳ ሰዎቻቸው እየታጀበ የሚከናውን ድርጊት ነው። የርስ በርስ ጦርነት እንዲካሄድ የሚያስችለው ደግሞ ሁሉም የርስ በርስ ጦርነቶች በህዝብ ጥቅም ስም ወይም በሃገር ሉዓላዊነት ስም መደረጉ ነው።

እኔ ለአንተ ከሱ የተሻልኩ ነኝ ወይም እኔ ከሱ የበለጠ ለሃገር ተቆርቋሪ ነኝ በሚሉ ወገኖች አነሳሽነት የሚፈጠር ቀውስ ነው። አንተ የሚሉትን ህዝብ ግን ማዳመጥ የማይችሉ ግብዞች ስራ ውጤት ነው። ካልሆነማ ሁላችንም ለህዝብና ለሃገር ካሰብንማ የህዝብን ደም ከሚያፈስ የመፍትሄ ሃሳብ ወጣ ባልን ነበር ። የፖለቲካ መፍቻችን የሰውን ልጆች ክቡር ህይወት ሊሰጥ የማይገባ እስከሆነ ድረስና በጋራ ሃገራዊ ጥቅምና ትርፍ እስካላስገኘ ድረስ ለሃገር ብዬ ነው ለህዝብ ብዬ ነው የሚሉት የፕሮፓጋንዳ ሃረጎች ትርጉም የላቸውም።

ስለዚህም ሃገራችንን የምንወድ ኢትዮጵያውያን ስለኢትዮጵያ ህዝብ ወይም ስለሃገራችን ህዝብ አንድነት የምንጨነቅ ሁሉ ዛሬ ከሁሉም አቅጣጫ  እየተመታ ያለውን የጦርነት ከበሮ ማስቆም ታሪካዊ ግዴታ አለብን ። የሚካሄደው ጦርነት ባህርይን ጠንቅቆ መገንዘብና በውንድማማቾች መካከል የሚደረገው ጦርነት ማንም በአሸናፊነት ቢወጣ ኢትዮጵያዊነት በቂምና በቁርሾ ላይ ሊያብብ እንደማይችል መረዳት ተገቢ ይሆናል። ጦርነት አምባገነኖችን ብቻ ከስልጣን አውርዶ የሚቆም ክስተት አይደለም ማህበራዊ እሴትን የማናጋት ባህርዩ ከፍተኛ ነው። በተለይ ምንም እንኳን በስልጣን ላይ ያሉ አምባገነኖች በሚፈጥሩት ደባና የስልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም በምክንያትም የተደገፈ ይሁን ያለምክንያት ጦርነቶችን መጫር ወይም መተናኮስ ባህሪያቸው ቢሆንም መንግስታቱ አምባገነኖች በመሆናቸው ብቻ በዘለቄታ ብሄራዊ ጥቅማችን ላይም ጭምር ከለየላቸው የሃገራችን ጠላቶች ጋር አለመቆማችንን    ማረጋገጡ አስፈላጊ ይሆናል፡

ስራቱ ከጊዜ ወደጊዜ ከመሻሻል ይልቅ እየዘቀጠና  በተለይም በተወሰኑ እኛ ብቻ አዋቂዎች ብለው በሚመጻደቁ ጥቂት ቡድኖች የማእከላዊነት አመራር  ወይም ሃላፊነት የጎደለው አክሂድ እየሄደ መሆኑ ግልጽ ነው። ሃላፊነት የጎደለው ስንል ደግሞ ለሰው ልጅ ህይውት ከሚሰጠው ክብርና ግምት አንስቶ ስለራሱም የወደፊት ህልውና ማሰብን ጭምር የሚያመለክት ቢሆንም በ እብሪትና በማን አለብኝነት የሚፈጥራቸውን ቀውሶች በሙሴ ህግ እጅን የቆረጠ እጅ አይንን ያጠፋ አይን ለሃገር ፖለቲካ መፍቻ ምላሽ ለመስጠት ከመሞከር ይልቅ ሃላፊነት የተሞላበትና የሚከፈለውም መስዋእትነት ዘለቂታና አስተማማኝ ውጤት ሊያመጣ እንዲችል ከጦርነት ባሻገር ያሉ ህዝባዊ ትግሎች እንደገና ሊፈተሹ ይገባል። ሊሎች የትግል ስልቶች የህይወት መስዋእትነት አያስከፍሉም ማለት እንዳልሆነ ባለፉት አመታት በተግባር አይተነዋል።  መስዋእትነቱ በጋራ

መቆምን አስተምሮአል በጋራ በአንድ እስርቤት መከራን በመካፈል ለጋራ ትግል አነሳስቶአል። በህዝቦች መካከል ያለውን ግንኙነት በሰከነ መንገድ ለማየት አስችሎአል። የስራቱ ደጋፊዎችን ጭምር ልባቸውን አሸፍቶአል። በተቃዋሚነት የተሰለፈው ጎራ ከድክመቱ አንሰራርቶ በጠንካራ አመራር  በስልት የተደገፈና  ህዝባዊ እምቢተኝነትን ትግል እያዳበረ ከሄደ የሃግራችን ትንሳኤ እሩቅ አይሆንም።

ስለዚህም በምንም መልኩ ቢሆን ለሃገራችን የምንጨነቅ ሁሉ ዳግም በሃገራችን የርስ በርስ ጦርነትም ሆነ በውጭ ሃይሎች በሚቃጣብን ወረራ  የኢትዮጵያዊ ወገን አስከሬን መሳለቂያችን ወይም ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ በማዋል ሃገራችን የምንወድ ለህዝባችን የቆምን አድርገን እራሳችንን ከቆጠርነው አሁንም እራሳችንን መመርመር የሚያስፈልግ ይመስለኛል።

የአምባገነኑን ስርዓት ለመታገል በተለያየ አቅጣጫ የተሰለፉ ወገኖች  ወይም በዚያች ሃገር ውስጥ  ማንኛውም አይነት ህዝብን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን የሚያነሱ ክፍሎች ከሌሎች ተመሳሳይ ችግር ካላቸው ወገኖች ጋር ቢያንስ በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው የጋራ ሃገራችንን እጣ ፈንታ ላይ ለመወያየት የሚያስችል ወኔና ድፍረት ከሌላቸው ከጦርነት የሚያገኙት ፍርፋሪ የወገኖቻቸውን ሰቆቃ ብቻ ነው።

እውነታው ዛሬ ህዝብ በስራቱ ተንገሽግሾአል። ስራቱም ብቻ ሳዪሆን ደጋፊው ጭምር ይህ ስራት መበስበሱንና መለውጥ ያለበት መሆኑን ዪፈልጋል።  ህዝብ ያጣው አንድ ነገር ነው፡ ስራቱን ተክቶ ሃገርን ለመምራት የሚችል የብዙዎችን ኢትዮጵያውያንን ጥያቀዎች ማእከል ያደረገና ሊዪነቶችን በበሰለ የፖለቲካ ጥበብ መፍታት የሚችል፡ የሃገሪቱን ሏላዊነት ለማስጠበቅና የኔ ብቻ መንገድ ከሚል እብሪት የጸዳ የፖለቲካ ሃይል ነው። ዛሬ ሁሉም እብሪተና በሆነበትና በኔ መንገድ ብቻ በሚል ፬ ድርጂት ወይም ስብስብ  ባለበት የሃገሩን ደህንነት በግርግር ለማንም አሳልፎ ላለመስጠት ሲል ብቻ በአምባገነኖች መዳፍ እየተደቆሰና መስዋእትነት እየከፈለ ይገኛል። በባህር ማዶ  ወይም በሃገር ውስጥ ተቀምጦ ተጨቁነሃል ተበድለሃል እያለ ብሶቱን የሚነግረውን አይደለም የሚፈልገው። ብሶቱን በህይወት ተሞክሮ ያውቀዋል፡ በዚህም ሆነ በዚያ ገፈቱን በቀጥታ እየተጎነጨው ነው። ያውቀዋል። ያጣው እምነት ነው። ብዙ ሲታለል የኖረ ህዝብ ነው። በስሙ ስንት ነገር እንደተሰራ ያውቃል። ዛረ ትውልዱም እየተቀየረ ሲመጣ የሃገር ፍቅር፡ የመስዋእትነት ልኩን እየተገነዘበም ይመጣል ። የኢንፎርሜሽን ዘመን በመሆኑም ብዙ ዪነጋገራል። በአጠቃላይም ትውልዱ የተሻለ ስራአት መምጣት እንዳለበት ቢፈልግም ስራቱን ለማምጣት በሚታገሉ ሃይሎች ላይ ኮንፊደንስ ገና አላደበረም ። እነሱም ቀልቡን በሚገባ አልሳቡትም። ለአንድ አላማ ቆመናል እያሉ በየቀኑ እየትማማሉ ተመልሰው እሳትና ጭድ ሆነው ሲታዩ እምነቱ ከየት ይመጣል፤ ለዚህም ነው መፍትሄው አንድብቻ የሚሆነው። በሃገራችን ለውጥ እንዲመጣ አምባገነኑም ስራት እንዲወገድ ያገባኛል የሚሉ ሁሉ በየፊናቸው የሚያደርጉትን ሩጫ አቁመው በጠረጴዛ ዙሪያ ተገናኝተው የልባቸውን መነጋገርና መተማመን ሲፈጥሩ ብቻ

ነው። መሪ ነን ባዮች በማይተማመኑበት መንደር ህዝብ እንዲያምናቸው መጠበቅ ሞኝነት ነው። ለዚህም ነው ይህ ባልለየበት ሁኔታ በየትኛውም በኩል የሚጎሰመውን የጦርነት አታሞ አጥብቀን ልናወግዘው የሚገባን።

ጦርነት ምንጊዜም የህዝብ ምርጫ አይደለም። ጦርነት ምንጊዜም በህዝብ ስም ተለውሶ የሚቀርብ መርዝና በጥቂቶች ለጥቂቶች ሲባል የሚደረግ እኩይ ተግባር ነው።

ጊሼይ ጊሻ

***http://www.ethiopanorama.com***

፥